# እውነት

## እውነት ምንድነው?

ይህ ጥያቄ ባለቤት አለው፦ ከእኛ በፊት ጠያቂ አለው፦ ጲላጦስ ይባላል።

“ጲላጦስ፦ እውነት ምንድር ነው? አለው። ይህንም ብሎ ዳግመኛ ወደ አይሁድ ወጥቶ፦ እኔስ አንዲት በደል ስንኳ አላገኘሁበትም።” (ዮሐንስ 18፥38)

ጥያቄው የቀረበው ለኢየሱስ ነበረ፤ ጠያቂው ጥሩ ጥያቄ አቅርቧል፤ የጠየቀውም መልስ ያለውን ነው። ኢየሱስ በጊዜው ምንም ያላለው አስቀድሞ መልሶ ስለነበረ እንደሆነ አስባለሁ።

“ኢየሱስም፦ እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፤ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም።” (ዮሐንስ 14፥6)

የወንጌሉ ፀሐፊ አስቀድሞ 'እውነት' በኢየሱስ እንደሆነ ጽፏል።

“ጸጋና እውነት ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ሆነ።” (ዮሐንስ 1፥17)

ጳውሎስም “በእርግጥ ሰምታችሁታልና፥ እውነትም በኢየሱስ እንዳለ በእርሱ ተምራችኋል፤” ብሏል። (ኤፌሶን 4፥21)

እውነት ኢየሱስ ነው!

እውነት በኢየሱስ ነው!

## የእግዚአብሔር አላማ ከእውነት አንጻር

እግዚአብሔር ለሰዎች ያለው አላማ እንዲድኑ ነው!. ከመዳን የሚቀድም ወይም የሚበልጥ ነገር እንደሌለ እረዳለሁ! ለእኛ ለአማኞች ደግሞ ያለው አላማ "እውነቱን ወደ ማወቅ" እንድንደርስ ነው!.

ሐዋርያችን ምን እንዳለ ይመልከቱ፦

“ሰዎች ሁሉ ሊድኑና እውነቱን ወደ ማወቅ ሊደርሱ በሚወድ በእግዚአብሔር በመድኃኒታችን ፊት መልካምና ደስ የሚያሰኝ ይህ ነው።” (1ኛ ጢሞቴዎስ 2፥3-4)

ስለዚህ እግዚአብሔር በእያንዳንዳችን ሕይወት በሥራ ላይ ነው። መዳናችንም እውነትን ማወቃችንም በፊቱ መልካምና ደስ የሚያሰኝ ነው።

ጳውሎስ ለኤፌሶን ሰዎች የጻፈው ነገር ተመሳሳይ አሳብ አለው።

“ሁላችን የእግዚአብሔርን ልጅ በማመንና በማወቅ ወደሚገኝ አንድነት፥ ሙሉ ሰውም ወደ መሆን፥ የክርስቶስም ሙላቱ ወደሚሆን ወደ ሙላቱ ልክ እስክንደርስ ድረስ፥ ቅዱሳን አገልግሎትን ለመሥራትና ለክርስቶስ አካል ሕንጻ ፍጹማን ይሆኑ ዘንድ።” (ኤፌሶን 4፥12-13)

"ሁላችን የእግዚአብሔርን ልጅ በማመንና በማወቅ ወደሚገኝ አንድነት፥ ሙሉ ሰውም ወደ መሆን፥..." ይህ ወሳኝ አሳብ ነው፤ የእግዚአብሔርን ልጅ ማመን እና ማወቅ።

በአንድ ሰው ሕይወት የሚቀድመው እምነት ነው። ለማመን የሚያበቃው ደግሞ የእግዚአብሔር ቃል ነው! (ሮሜ 10፥17)

ኢየሱስን ከማመን ቀጥሎ በሕይወታችን በወጥነት የሚቀጥለው እውነትን ማለትም ኢየሱስን ማወቅ ነው። ኢየሱስን በማመን የዳነ ሰው ኢየሱስን በማወቅ ሙሉ ሰው ወደ መሆን ያድጋል ማለት ነው!.

## እውነትን የማወቅ ጥቅሞች፡-

### 1) ዕድገት (Spiritual growth)

እውነትን (ኢየሱስን) ወደ ማወቅ ስንደርስ ሙሉ ሰው ወደ መሆን እናድጋለን። እውነትን (ኢየሱስን) ማወቅ መንፈሳዊ ብስለት ያመጣል።

“ሁላችን የእግዚአብሔርን ልጅ በማመንና በማወቅ ወደሚገኝ አንድነት፥ ሙሉ ሰውም ወደ መሆን፥ የክርስቶስም ሙላቱ ወደሚሆን ወደ ሙላቱ ልክ እስክንደርስ ድረስ፥ ቅዱሳን አገልግሎትን ለመሥራትና ለክርስቶስ አካል ሕንጻ ፍጹማን ይሆኑ ዘንድ።” (ኤፌሶን 4፥12-13)

አሁን የምናየው ህፃንነት (immaturity) ኢየሱስን በማወቅ ስር ካለመስደድ የመነጨ ነው። መፍትሔው ደግሞ እውነትን ማወቅ ነው።

### 2) ነፃነት

እውነትን (ኢየሱስን) ስናውቅ እውነትን ማወቅ የሚሰጠውን ነፃነት ማጣጣም እንጀምራለን።

“እውነትንም ታውቃላችሁ እውነትም አርነት ያወጣችኋል አላቸው።” (ዮሐንስ 8፥32)

በመጀመሪያ ኢየሱስ እንደዚህ የተናገረው ለአማኞች መሆኑን እናስተውል። ((ዮሐንስ 8፡31) እውነት አርነት ያወጣል! ለምሳሌ፡- ከፍርሃት፣ ከይሉኝታ ከሀፍረት፣ ... ነፃ ያወጣናል! ስለዚህ ከመዳን ቀጥሎ እውነትን ወደ ማወቅ መድረስ ይኖርብናል።

ጳውሎስ 'ያመነውን ኢየሱስን በማወቅ' ነፃ ስለወጣ ስለእርሱ መከራ መቀበል እንዳላሳፈረው ጽፏል።

“ስለዚህም ምክንያት ይህን መከራ ደግሞ ተቀብዬአለሁ፥ ነገር ግን አላፍርበትም፤ ያመንሁትን አውቃለሁና፥ የሰጠሁትንም አደራ እስከዚያ ቀን ድረስ ሊጠብቅ እንዲችል ተረድቼአለሁ።” (2ኛ ጢሞቴዎስ 1፥12)

"አላፍርበትም፤ ያመንሁትን አውቃለሁና" ያላፈረው ለምንድነው? ያመነውን በማወቅ ስር ስለሰደደ ነበር።

## የአማኞች ተልዕኮ

- **እውነትን በቅንነት ማቅረብ**

የአማኞች ዋና ተልዕኮ … የወንጌልን እውነት ሰዎች ጋር ማድረስ ነው።

“በእነርሱም መካከል የሕይወትን ቃል እያቀረባችሁ በዓለም እንደ ብርሃን ትታያላችሁ” (ፊልጵስዩስ 2፥16) ስለዚህ አማኞች እውነትን መመስከር ይኖርብናል!

- **እውነትን በፍቅር መያዝ**

ሐዋርያው “ነገር ግን እውነትን በፍቅር እየያዝን በነገር ሁሉ ወደ እርሱ ራስ ወደሚሆን ወደ ክርስቶስ እንደግ፤” ብሎአል። (ኤፌሶን 4፥15)

በእኛ ዘመን የስህተት ትምህርት እና አሰራር በዝቶአል። መፍትሄው ደግሞ እውነትን ማወቅ ነው።

ሀሚልተን የተባለ ጸሐፊ ``እኛ ከስህተት የምንጠበቅበት መንገድ ስህተትን በማወቅ ሳይሆን እውነትን በፍቅር በመያዝ እና ህያው የሆነውን ክርስቶስን በነፍሳችን ፊት በማድረግ ነው`` እንዳለ።[1]

- **እውነት ላይ ሸፍጥ አለመስራት**

“ለእውነት እንጂ በእውነት ላይ ምንም ለማድረግ አንችልምና።” (2ኛ ቆሮ 13፥8)

- **ለእውነት መጋደል**

ሐዋርያው ጳውሎስ … ሰዎች እውነትን (ክርስቶስን) እንዲያውቁ ተጋድሏል!.

“ልባቸው እንዲጸናና፥ በፍቅርም ተባብረው በማስተዋል ወደሚገኝበት ወደ መረዳት ባለ ጠግነት ሁሉ እንዲደርሱ የእግዚአብሔርንም ምሥጢር እርሱንም ክርስቶስን እንዲያውቁ እጋደላለሁ፤” (ቆላስይስ 2፥2)

ይህ መልካም ገድል ነው። እርሱም በመጨረሻው መልእክቱ "መልካሙ ገድል" ብሎ ይገልጸዋል።

---

[1] ሀሚልተን ስሚዝ የኤፌሶን መልእክት ማብራሪያ ገጽ 68

“መልካሙን ገድል ተጋድዬአለሁ፥ ሩጫውን ጨርሼአለሁ፥ ሃይማኖትን ጠብቄአለሁ፤” (2ኛ ጢሞቴዎስ 4፥7)

አሁንም እኛ አማኞች ... እውነት (ክርስቶስ) እንዲታወቅ መጋደል ይኖርብናል!. አማኞች መልካሙን ገድል በመጋደል ራሳችንን ካልጠመድን ትርፍ ለሌለው ነገር መድከማችን አይቀርም።

- **ለእውነት ጸንቶ መቆም**

“የወንጌልም እውነት በእናንተ ዘንድ ጸንቶ እንዲኖር ለአንድ ሰዓት እንኳ ለቅቀን አልተገዛንላቸውም።” (ገላትያ 2፥5)

## ሰዎች እውነትን ወደ ማወቅ ለምን አይደርሱም?

እውነት ራሱን ሰውሮ "ፈልጉኝ" አላለም። እውነት የማይደረስ አይደለም። ባልተወሳሰበ መንገድ በመጽሐፍ ቅዱሳችን ተገልጿል። እውነት ራሱን ግልጥ ያደረገበትን መጠን ለማሳየት አንድ ነገር እናንሳ። የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት የተጻፉት "በኮይኔ" ግሪክ ነው። ይህ ቋንቋ ያልተማረ ሰው እንኳን የሚግባባበት ቀላል ግሪክኛ ነበረ። አሁንም ቢሆን የመጽሐፍ ቅዱስን መልእክት (ክርስቶስን) በቀላሉ ለማቅረብ ብዙ ነገሮች ተሞክረዋል። ታዲያ ሰዎች ለምን ወደ እውነት አይደርሱም?

### ከማያምኑ ሰዎች እንጻር፦

**1) የእውነትን መንፈስ አለመታዘዝ**

መንፈስ ቅዱስ የእውነት መንፈስ ነው። የእርሱ ዋናው ሥራ ሰዎችን ወደ እውነት (ወደ ኢየሱስ) መምራት ነው!

“ግን እርሱ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል፤ የሚሰማውን ሁሉ ይናገራል እንጂ ከራሱ አይነግርምና፤ የሚመጣውንም ይነግራችኋል።” (ዮሐንስ 16፥13)

የእርሱን ምስክርነት እምቢ የሚሉ ሰዎች ወደ እውነት አይደርሱም!

**2) እውነትን መቃወም**

እውነት ሲነገር የሚቀበሉት እንዳሉ ሁሉ የሚቃወሙትም አይጠፉም፤ በየዘመናቱ የሆነው ይህ ነው። እውነትን የሚቃወሙ ሰዎች ወደ እውነት አይደርሱም። ለሌሎችም እንቅፋት ናቸው።

“እውነትን በዓመፃ በሚከለክሉ ሰዎች በኃጢአተኝነታቸውና በዓመፃቸው ሁሉ ላይ የእግዚአብሔር ቍጣ ከሰማይ ይገለጣልና፤” (ሮሜ 1፥18)

ይህን ክፍል በመደበኛ ትርጉም እንየው፡-

“በክፋታቸው እውነትን ዐፍነው በሚይዙ፣ በዐመፃቸውና በክፋታቸው ሁሉ ላይ የእግዚአብሔር ቍጣ ከሰማይ ይገለጣል፤” — ሮሜ 1፥18 (አዲሱ መ.ት)

"እውነትን ዐፍነው የሚይዙ" ማለቱ አልገረማችሁም?

በሐዋርያው ጳውሎስ አገልግሎት ከገጠሙት ተቃዋሚዎች መካከል የተሰሎንቄ ሰዎች ይጠቀሳሉ።

“አይሁድ ግን ቀንተው ከሥራ ፈቶች ክፉ ሰዎችን አመጡ ሕዝብንም ሰብስበው ከተማውን አወኩ፥ ወደ ሕዝብም ያወጡአቸው ዘንድ ፈልገው ወደ ኢያሶን ቤት ቀረቡ፤” (ሐዋርያት 17፥5)

እነዚህ ሰዎች ለእውነት የሚሆን ልበ ሰፊነት የሌላቸው ናቸው። በአንጻሩ ደግሞ ለእውነት ጥሩ ልብ ያላቸው የቤሪያ ሰዎችም ነበሩ።

“እነዚህም በተሰሎንቄ ከሚኖሩት ይልቅ ልበ ሰፊዎች ነበሩና፡- ነገሩ እንደዚሁ ይሆንን? ብለው ዕለት ዕለት መጻሕፍትን እየመረመሩ ቃሉን በሙሉ ፈቃድ ተቀበሉ።” (ሐዋርያት 17፥11)

**ከአማኞች አንጻር፡-**

**3) በልዩ ልዩ ምኞቶች መያዝ እና የኃጢአት ልምምድ**

አማኞች ነፍሳችን በሌላ ነገር ከተያዘች ለእውነት የሚሆን ልብ አይኖረንም! ጳውሎስ ምን እንዳለ እንመልከት፡-

"ኃጢአታቸው የተከመረባቸውን #በልዩ #ልዩ #ምኞትም የሚወሰዱትን ሁልጊዜም እየተማሩ እውነትን ወደ ማወቅ ሊደርሱ ከቶ የማይችሉትን ሞኞችን ሴቶች የሚማርኩ፥ ከእነዚህ ዘንድ ናቸውና።" —2ኛ ጢሞቴዎስ 3፥6-7።

ይህን አይነት የሕይወት ዘይቤ ያላቸው አማኞች የቱንም ያህል ቢማሩ እውነትን ወደ ማወቅ እንደማይደርሱ ክፍሉ ይናገራል፡፡ እንደዚህ አይነት የነፍስ ቁመና ያላቸው ሰዎች ለስህተት ትምህርት እና አሰራር ተጋላጭ ናቸው። (2ኛ ተሰሎንቄ 2:9-12)

**4) እውነትን ምርጫ አለማድረግ**

ጳውሎስ እውነትን ችላ ስለሚሉ ሰዎች ጽፏል።

"ሕይወት የሚገኝበትን ትምህርት የማይታገሡበት ዘመን ይመጣልና፤ ነገር ግን ጆሮቻቸውን የሚያሳክክ ስለ ሆነ፥ እንደ ገዛ ምኞታቸው ለራሳቸው አስተማሪዎችን ያከማቻሉ። እውነትንም ከመስማት ጆሮቻቸውን ይመልሳሉ፥ ወደ ተረትም ፈቀቅ ይላሉ።" (2ኛ ጢሞቴዎስ 4፥3_4)

ፈቃዳቸውን ተጠቅመው እውነትን ከመስማት ጆሮቻቸውን የሚመልሱ፥ ወደ ተረት፣ ወደ ትውልዶች ታሪክ፣ ፈቀቅ የሚሉ ሰዎች አሉ። ሐዋርያው ``እንደ ገዛ ምኞታቸው ለራሳቸው አስተማሪዎችን`` እንደሚያከማቹም ጽፎአል። እነዚህ ሰዎች ወደ እውነት የመድረስ እድላቸው ጠባብ ነው።

በርናባስ ዘመነ